# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(አንድነት/United)


የካቲት 27 ቀን 2008 ዓ. ም
March 6, 2016

# የዓድዋን በዓል ስንዘክር ዛሬንም እናስብ!

ዓድዋ በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ ክፍለ ሀገር የምትገኝ ትንሽ ወረዳ ስትሆን፣ ስሟ ግን ግዙፍ፣ በዓለም ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ የተሻገረና የታሪክ ተመራማሪዎችን ዓይን የሳበች ታላቅ ባለታሪክ ቦታ ናት። አድዋ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ቀንዲል የበራችበት ታላቅ ቦታ።

የዓድዋ ድል አያት ቅድመ-አያቶቻችን የዛሬ አንድ መቶ ሃያ ዓመት የጣሊያንን ጦር ወራሪ ድል ያደረጉበት፣ እኛ ዛሬ በኩራት አንገታችንን ቀና አድረገን እንድንሄድ ክቡር ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡበት ታሪካዊ የነፃነት ምልክታችን ነው። ከእኛ ከኢትዮጵያውያንም አልፎ መላውን የጥቁር ዘር በኩራት እንዲናገር ያስቻለ ገድል ነው።

ሰማዕቶቻችን ዘርና የሥልጣን ጥቅም ሳያግዳቸው፣ ከአገሪቱ አራቱም ማዕዘናት ተጠራርተው፣ የተኮራረፉ ይቅር ለእግዚአብሔር ተባብለው፣ በአንድነትና በአንድ ልብ ለአገር ክብር በመዝመት ለነፃነታቸው ደማቸውን አፍስሰዋል፤ አጥንታቸውንም ከስክሰዋል። በየጦር ሜዳው ረግፈው እንደወጉና እንደባህሉ ሳይቀበሩ የአሞራ እራት ሆነው የቀሩ ሰማዕቶቻችን እኛ አሁን የምንተነፈስውን የነፃነት ንፁህ አየር በደማቸው አጥርተውልን አልፈዋል። በቅኝ-ግዛት የተገዙ አገሮች ማንነታቸው ጠፍቶባቸው እየተቸገሩ ባሉበት ዓለም ውስጥ፣ የእኛ የኢትዮጵያውያን ማንነት ግን ደም በተገበረለት ተጋድሎ ማንነታችን ተከብሮ ኖሯል፤ ይኖራልም።

በአፄ ምኒልክ ኃይለመለኮትና በባለቤታቸው በንግሥተ ነገሥታት ጣይቱ ብጡል መሪነት ቆራጡ የገበሬ ጦር በዘመናዊ መሣሪያ እስካፍንጫው የታጠቀውን የጣሊያንን ጦር ድል አድርጎ አኩርቶናል።


**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

ታዲያ ጀግንነት ይኮሩበታል እንጂ የሚወረስ ባለመሆኑ፣ አገራችን በጎሣ ፖለቲካ ተሰነጣጥቃ ህልውናዋ አፋፍ ጠርዝ ላይ በቆመበት በአሁኑ ስዓት፣ እንደ ዓድዋ ጀግኖቻችን የግል ችግራችንን ወደጎን ትተን በአንድነት ለአንድነት በመቆም ማንነታችንን እንደገና ማደስ ሲገባን፣ አገር-በቀል በሆኑ ባንዳ አምባገነኖች ከባዕድ መንግሥታትና ግብረ አበሮቻቸው ጋር በመመሳጠር ረቂቅ ፀረ-አንድነትና ፀረ-ሕዝብ ተንኮል በማካሄድ ለዘመናት ገኖና ተከብሮ የኖረውን ማንነታችን ለማጥፋት ጠንክረው እየሠሩ ናቸው። የእነዚያ የዓድዋ ጀግኖች ልጆችና የልጅልጆች በቋንቋ እንዳንግባባ፣ አብረን እንዳንበላና እንዳንጠጣ፣ ልብለልብ እንዳንገናኝና ወራሪ ጠላት ቢመጣም በጋራ አገራችንን እንዳንከላከል ጎሣን መሠረት ባደረገ የአገዛዝ ክልል ሸንሽነውን እርስ በእርስ እንድንጠራጠር እያደረጉን ነው። እነአሉላ አባ ነጋ፣ እነባልቻ አባ ነብሶና ሌሎችም ለአገር ነፃነትና ክብር ሕይወታቸውን የሰጡ ጀግኖቻችን አንገታቸውን ከመቃብር ቀና አድርገው ቢያዩን ምንኛ ያዝኑ ይሆን?

ዛሬ ሁሉም በየክልሉ የራሱን የጎሣ ቋንቋ ብቻ እንዲናገርና የወጣቱ ትውልድ አስተሳሰብ ከጠባብ ጎሠኝነት አልፎ ብሔራዊ አመለካከት እንዳይኖረው እየተደረገ ያለው ሆን ተብሎ ኢትዮጵያዊ ማንነትን ለማጥፋት መሆኑን ማጤን በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ኢትዮጵያውያንን እርስ በራሳችን እንዳንግባባ ለማድረግ ነው። ከአልተግባባን አብሮ መኖር አይቻልም። ለዚህም ነው የሚካሄድብን የከፋፍለህ ግዛው ተንኮል አገራችንንና ማንነታችንን ለማጥፋት እየተደረገ ያለ ርብርቦሽ በመሆኑ ልንዋጋው ይገባል የምንለው።

አምባገነኑ አገዛዝ በመላው የኢትዮጵያ ጀግኖች ደም የተገኘውን የዓድዋን ድል የክልል ድል ለማድረግ የማይጠነስሰው ተንኮል የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። ኢትዮጵያዊነትን ከታሪክ ማህደር ለመፋቅ አልያም ለማሳነስና ለማንኳሰስ፣ አኩሪ ድርጊት ሠርተው ያለፉ የጀግኖች አያቶቻችንን ገድል ከታሪክ ማህደር ለመፋቅና ታሪክ አልባ ለማድረግ የሚሸረብ ደባ ነው። ጣሊያን ከዚያ ውርደትን ከተላበሰ ሽንፈቷ በኋላ ይህን አድርጋው ቢሆን ኖሮ ጀግኖች አያቶቻችን በዓለም ዙሪያ፣ በአደባባይ የሀፍረት ሸማ ስላከናነቧት በመሆኑ ከቶውንም አይደንቀንም ነበር። ነገር ግን ይህ ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የሚደረገው ጥረት የእኛን ቆዳ በለበሱ አገር-በቀሎች የሚካሄድ በመሆኑ በጣም ያሳዝናል። ስለሆነም

እጅግ ልናስብበት ይገባል፤ ዘር ከልጓም ይስባል እንደሚባለው ክህደትም ይወረሳልና ይኸውና ልጆቻቸው በታሪክ ደገሙት።

ስለዚህ በየዓመቱ ዓድዋን እያከበርንና ጀግኖቻችን ያደረጉትን ገድል እያደነቅን መቀመጠ ነፃነታችንን ዘላለም ያስከብርልናል ማለት አይደለም።  እኛም እንደ አያቶቻችን በአንድ ላይ ሆ! ብለን በመነሳት ለዴሞክራሲና ለአገር አንድነት የሚደረገውን ትግል ሙሉ ድጋፍ ልንሰጠውና ልናጎለብተው ይገባል።

ዛሬ የኅብረተስቡ ትኩስ ኃይል የሆነው ወጣቱ ትወልድ በአገሩ ላይ የሥራ ዕድልና የመኖር ዋስትና በማጣቱ ሳይወድ በግድ አገሩን እየጣለ በመሰደድ ላይ ነው። በአገር ውስጥ የሚኖሩ ወጣቶችም፣ በምዕራባውያን ርካሽ ባህል ልክፍት አዘቅት ውስጥ እየገቡ ነው። በወጣት ዕድሜያቸው በልመና ሥራ፣ በሴተኛ አዳሪነት፣ ዕድሜያቸው በማይመጥነውና ባህላቸው  በማይፈቅደው ርካሽ ሥራም እየገቡ ነው።

ዛሬ በአገራችን ውስጥ የተንሰራፋው የከፋፍለህ ግዛው የጎሣ ፖለቲካ እኩይ ተግባሩና ትዕቢቱ ከፍተኛ ውጥረትና ፍጥጫ ላይ ደርሷል። መንግሥት ተብዬው ደግሞ ሥልጣኑን ላለማጣት ያለውን ኃይል ሁሉ እየተጠቀመ ሕዝባችንን በግፍ እየገደለ ነው።  በአሁኑ ወቅት ይኸው የበደል ፍጻሜ ይበልጥ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እየገባ  መጥቷል።

ዛሬ የአገራችን ኤኮኖሚ ደቆና ላሽቆ በርካታው የሀገራችን ሕዝብ የዕለት ጉርሱን ማሟላት ያለቻለበት ሁኔታ ላይ ነን።  በተፈጥሮ የአየር መዛባትና ኃላፊነት በጎደለው የሰው ሠራሽ ድርጊት ምክንያት በአገራችን የተከሰተው ረሃብ ሕዝባችንን እየጨረሰ ነው። የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ በረሃቡ ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመረባረብ ፋንታ፣ ለመብት ጥያቄ አቤቱታ የወጣን ሕዝብ ለጋ ህፃናትን እንኳን ሳይቀር በጥይት ይደበድባል፤ ይበልጥ እንዴት እንደሚጨፈጭፍም ስልት ሲቀይስ ይውላል።

ስለዚህ አገራችን እንዲህ ባለ አጣብቂኝ ችግሮች ውስጥ ባለችበት በአሁኑ ወቅት፣ የዓድዋ ጀግኖቻችንን ሰማዕትነት እያከበርን በስማቸው መኩራራት ብቻ ሳይሆን፣ ልዩነታችንን አቻችለን፣ ከድርጅታዊ ፍቅር ይልቅ የአገር ፍቅርን በማስቀደም በአንድነት ለአንድነት ቆመን አገራችንን ከገባችበት አዘቅት ውስጥ በማውጣት ሰላምና ዴሞክራሲ የሰፈነባት፣

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **Email Address**: **eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

የሁሉም ብሄረሰቦች የእኩልነት መብት የሚከበርባት አገር እንድትሆን የማድረግ ታሪካዊ ኃላፊነታችንን እንድንወጣ ኢሕአፓ (አንድነት) ዛሬም እንደወትሮው ጥሪውን ያቀርባል።

የሰማዕቶቻችንን ታሪክ በአንድነታችንና በትግላችን ተከብሮ ይኖራል!

**P.O.Box 91384**
**Los Angeles, CA 90009**
**Phone: 202- 241 2078**
**Email Address**: **eprp-democratic@eprp-ihapa.com**